# የኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው በቅርቡ የገቡ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ለመርዳት እየተረባረበ ይገኛል

የኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው በቅርቡ ከኢትዮጵያ የመጡ አዳዲስ ስደተኞች የመንግሥት ማረፊያ ቤቶች ወይም መጠለያዎች በመሙላታቸውና ችግሩ ከከተማው አቅም በላይ በመሆኑ ለቀናቶች በቶሮንቶ ከተማ መጠለያ ፊት ለፊት መንገድ ላይ እያደሩ ከፍተኛ ችግር የገጠማቸውን ሁኔታ ከሰማ በኋላ፤ የማህበሩ ፕሬዚዳንትና የክራይስስ ኮሚቴ አባሎች ሄደው ሁኔታውን ከተመለከቱና ካጣሩ በሁዋላ አስቸኳይ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው በማመን፤ የሚበሉት ምግብና ወሃ በማቅረብ፣ መጠለያ እንዲያገኙ በተለያዩ መጠለያዎች በመደወልና ቦታ በመፈለግ እንዲሁም የቶሮንቶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ጉዳዩን እንዲያውቀው በማድረግ የተጀመረው እርዳታ  የማህበሩን አባላትና ኢትዮጵያውያንን እንዲሰሙት በማድረግ ያልተቋረጠ ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ማህበርም 1950 ዳንፎርዝ አቬኑ የሚገኘውን ቢሮና አዳራሽ የመሰባሰቢያ ማዕከል በማድረግ አዲስ የመጡ ስደተኞችን በማስተናገድ መጀመሪያ ጊዜያዊ ማረፊያ እንዲያገኙ የኮሚኒቲውን አባላት እየጠየቁ እጅግ ቀናና ከፍተኛ የሆነ የትብብር መልስ በማግኘቱና ሕበረተሰቡ በጋራ ተረባርቦ በመርዳቱ እጅግ ከፍ ያለ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

በተለያዩ አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚችሉትን ያህል ሰው ለቀናቶች በቤታቸው አሳርፈው እያስተናገዱ ሲገኝ፤ በቶሮንቶም ከተማ እንደዚሁ በየቀኑ በቤታቸው በማሳደር፣ መኪና ያላቸው ስደተኞችን ከቦታ ቦታ በማዘዋወር የትራንስፖርት ችግርን የቀረፉ ሲሆን፣ ገሚሱ ምግብ ከቤቱ እየሰራ ማህበሩ ጽ/ቤት ድረስ በማምጣት እየመገቡና ሌላውም ከሬስቶራንት ምግብ በመግዛት እያመጣ እንዲመገቡ አድረገዋል፡፡ ሌሎችም ኢትዮጵያውያን የማህበሩን ጥሪ ሰምተው ጊዜያዊ መጠለያ በመፈለግ በነጮቹ ቤተክርስቲያን ጊዜያዊ መጠለያ እንዲያገኙ ሲያደርጉ፣ በራሳቸው ትራንስፖርት በየሆቴሉም እንዲያርፉ የሆቴሉ ማረፊያ ወጪ በመሸፈን ወገኖቻችንን እረድተዋል፡፡ መጠለያ ያጡትን ደግሞ ወደየቤታቸው በመውሰድም ያስተናገዱ የቦርድ አባላትና የክራይስስ ኮሚቴ (crises committee) አባሎች እንዲሁም የማከበሩ አባላትም መልካም ተግባር እጅግ አስደሳችና የሚያኮራ ነው፡፡

በማህበሩ ጽ/ቤትም ጉዳያቸውን የሚይዙ ጠበቆችን በመፈለግና በማገናኘት፣ አስፈላጊውን የመንግስት ፎርሞችን በመሙላት፣ የማህበሩን ኮምፒወተር እንዲጠቀሙ፣ ዶክመንቶችን ማተምና ማባዛት አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ፣ ሜዲካል ምርመራ ያሚያደርጉትን ቦታው በማድረስና የሚፈለገውን ሁሉ ለሟሟላት ሁሉም እየተረባረበ ይገኛል፡፡

ጠዋት ካደሩበት ቤት ሲመጡም የሰሞኑ ሞቃት አየር እንዳያደክማቸው በጽህፈት ቤቱ ቀዝቀዝ እንዲሉ ወሃ፣ ቡና እና ምግብ እንዲያገኙ እያደረገ ሲገኝ፣ ሻንጣዎቻቸውን ተሸክመው መዞር አስቸጋሪ በመሆኑ በማህበሩ ጽ/ቤት እንዲያሳርፉና የሚፈልጉት ነገር ሲኖር እያወጡ አስተማማኝ መጠለያ እስኪያገኙ ድረስ ተቀምጦላቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ችግሩን የሰሙ ኢትዮጵያውያን በማህበሩ አካውንት ለአዲስ መጪዎቹ እርዳታ የሚውል የገንዘብ አስተዋጾ በኢትራንስፈር ያስገቡትን ሁሉ በአጠቃላይ በእጅጉ ያመሰግናል፡፡ የማህበሩ ጽህፈት ቤትም ከጠዋት አንስቶ እስከ ምሽቱ አራት እና አምስት ሰዓት ድረስ ክፍት ሆኖ ሲያገለግል ይህ የመጀመሪያው ጊዜ ነው፡

በማህበሩ አስተባባሪነት የቦርድ አባላት ለችግሩ ያጋራ መፍትሄ ለማግኘት ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ባለሞያዎችና ካናዳዊ ጋር የዙም ስብሰባ በማድረግ ውይይት ማካሄዱም ታውቋል፡፡

በመጠለያ ፊት ለፊት ከነበሩት ጋር የኬንያ ስደተኞችም መጠለያ አጥተው ተቸግረው ኢ/ያኑ ወደ ማህበሩ ጽህፈት ቤት ሲመጡ እኛም ተቸግረናል ብለው እርዳታ በመጠየቃቸው ወደ 20 የሚጠጉ የኬንያ ዜግነት ያላቸውንም አብረው በማምጣት እንዲያርፉ እንዲመገቡና መጠለያ እንዲያገኙ ተደርገዋል።

እንዲሁም የችግሩን መጠን በመገንዘብ ሁለት የዩኒየን ሰዎች መጥተው ከኢትዮጵያ ማህበር ጋር በመነጋገር የጊዜያዊ መጠለያ በማፈላለግና የስሊፒንግ ባግ በመግዛት እንዲሁም የገነዘብ እርዳታ በማድረግ ትብብራቸውን አሳይተዋል። የዌንጌላዊ ቤተክርስቲያንም ትብብራቸውን የገንዘብ አስተዋጽኦ በማድረግ ተባብረዋል።

ከቶሮንቶ ከተማ መንግሥት አቅም በላይ የሆነውን ችግር የካናዳ ፌዴራል መንግሥት አንድ ነገር እስኪያደርግ ድረስ የማህበሩ ጽህፈት ቤትና አባላት እርዳታም እንደሚቀጥል እያስታወቅን፤ ይህ ከዚህ በፊት አጋጥሞን የማያውቀውን ችግር ለማቃለል የማህበሩ አባላትና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ከቤታቸው ምግብ እየሰሩ ምሳ ወይም እራት በማምጣታቸውና በመመገባቸው ከማህበሩ ጋር በመሆን የተደረገው ትብብርና ሥራ ማህበራችንን ያኮራና ያስደሰተ መሆኑ የኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው ጽህፈት ቤት የህዝብ ግንኙነት ክፍል ያስታውቃል፡፡

ጁን 5 ቀን 2023 ዓ/ም